# አዘራፊና ዘራፊ ሲበላ ባለ አገር ይቀላውጣል !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)








## ማስታወሻ:

*ወያኔ በጎሳ በረት ያጎራቸው: የአስተሳሰብ ድንክዬዎች፤ በታጎሩበት የጎሳ በረት ውስጥ ሆነው ሲያጓሩ ስንሰማ፤ እኛ እንደነሱ በዘረኝነት ታጥረን ሳይሆን፤ በኢትዮጵያዊነት ማማችን ላይ ሆነን ቁልቁል ስንመለከታቸው፤ እያንጋጠጡ የሚተፉት ሁሉ: ተመልሶ ባፋቸው እየገባ: አረፋ ሲደፍቁ ስናይ፤ አዘንላቸው እንጂ አልጨከንባቸውም፤ ታዘብናቸው እንጂ አልከፋንም፤ ይበልጥ አበረቱን እንጂ ክንዳችን አልዛለም፤ ብዕራችን አንደበቱ ሰላ እንጂ አልተዘጋም::*
*እኛ የምንጽፈው ስለ አገር አንድነት፤ ዕኩልነት፤ ፍቅርና ብልጽግና ሲሆን፤ እነሱ የሚጭሩት ስለ ክልል (መንደር)፤ ጎሳ፤ ዘረኝነት፤ ስርቆትና ጥላቻ ነው ::*
*የእምዬ ኢትዮጵያ ልጆች ሆይ፤ ጻፉ! ጻፉ! አሁንም እንደገና ጻፉ! እንጻፍ! አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ የሚነገርላትና፤ ብዙ የሚጻፍላት ታሪክ ያላት እንጂ፤ የሚታፈርባት አገር አይደለችም::*
*ሃቅ በተጻፈ ቁጥር የአሳሞችን ሆድ ቀትሮ፤ በንዴት እያበገነ: ጨጓራቸውን ይመልጣል:: የእምዬ ኢትዮጵያን ልጆች ደግሞ: ዕንባቸውን አብሶ፤ አንጀታቸውን አርሶ፤ አይምሯቸውን በማደስ ለአገራቸውና ለመብታቸው ዘብ እንዲቆሙ ያደርጋልና ሳትታክቱ ጻፉ፤ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ቀርቧልና!!*

## መንደርደሪያ:

- *« Making people to fear and depressed keep them silent and hopeless and accept the situation as normal even if it is worst."*

*"ሰዎችን እንዲፈሩና እንዲሸበሩ ማድረግ፤ ዝም እንዲሉና ተስፋ ቆርጠው ያለውን ጨቋኝና መጥፎ ሥርዐት እንደ ጤናማ አስተዳደር ተቀብለው እንዲኖሩ ያደርጋል"::*

*ወያኔዎችም እያደረጉ ያሉት ይህንኑ ነው፡፡ ግን እስከመቼ?*

- *« On gouverne mieux les hommes par leur vice que par leur vertu »*

*« ሰዎችን በደካማ ጎናቸው በመጠቀም ማለት፤ ሆዳምን በሆዱ፤ ጠጪን በመጠጥ፤ ሴሰኛን በሴሱ፤ ዘማዊን በዘማዊነቱ፤ እንደበርሜል እያንከባለሉ መግዛት » ፡፡*

*ወያኔዎች በስልጣን ለመቆየት ሲሉ እያንዳንዱን ደካማ ፍጡር፤ በደካማ ጎኑ ሰርገው በመግባት ቦርቡረው ካነቀዙት በኋላ፤ ከዚያ እንደራሳቸው ዓሣ ዓሣ እንዲሸት አድርገው፤ በሰዎች ዘንድ እንዲጠላ ካደረጉት በኋላ፤ እንዳሻቸው ይጋልቡታል ፡፡ ከዚያ በኋላ ደፍሮ እንቢ የሚልበት ወኔ ስለማይኖረው፤ የድመት ዕውር አድርገው እስከ መቃብር ይጎትቱታል፡፡*

*(The useful idiots of EPRDF) ደደብት የወያኔ መጠቀሚያዎች ከየፖለቲካ ድርጅቱ፤ ከየጎሳውና ከየሃይማኖት ዘርፉ፤ እየሆኑ የምናየው ይህንኑ ነው፡፡*

- *" Only two things are infinite, the universe and human stupidity, and I am not sure about the former."*
  *Albert Einstein*

*" ሁለት ነገሮች ብቻ ማብቂያ የላቸውም፤ እነሱም፤ የተፈጥሮ (የዓለም) ና የሰው ልጆች ደደብነት ሲሆኑ፤ ስለ ተፈጥሮ ደደብነት ግን እርግርጠኛ አይደለሁም "፡፡*
*አልበርት አነስታይን*

- *" Don't fear death so much but rather the inadiquate life."*
  *Bertolt Brecht*

*" ሞትን ይህን ያህል አትፍራ፤ ይልቅስ መፍራት አጓጉል (ጎስቋላ) ኑሮ መኖርን ነው " ፡፡*
*በርቶል ብሬች*

- *" Every man has the right to risk his own life in order to save it."*
  *Jean Jacques Rousseau*

*"እያንዳንዱ ሰው ሕይወቱን ሊያድናት ከፈለገ መስዋዕትነትን መክፈል የግድ ይለዋል"*
*ዣን ዣክ ሩሶ*

## መግቢያ:

*መሬት ዕትብት ነው: ከወላድ እናት ጋር የሚያስተሳስር የፍቅር ገመድ፤ መሬት ጋናሻና ጦር ነው : ከአያት ከቅድም አያት ተወርሶ: ጠላትን ድል የሚነሱበት መሳሪያ፤ መሬት ማተብ ነው: የሃይማኖቱ መግለጫ፤ የዕምነቱ ማምለኪያ ቦታ፤ ወይም የአላህ ስም የሚጠራበትን: መስጊድ ማስከበሪያ፤ መሬት ልጅ ነው: ዕድሜ ገፍቶ ጉልበት ሲደክም: ምርኩዝ ሆኖ የሚደግፍ፤ መሬት ጃንጥላ ነው: ከጠራራ ፀሐይ፤ ከደፍ ዝናብ እራስን መከለያ፤ መሬት ፍቅር ነው: ያመረቱትን ከወገን ጋር አብሮ የሚያቋድስ፤ መሬት ገመና ነው: የራስን ምስጢር መሸሸጊያ፤ መሬት ትዳር ነው: ባልና ሚስትን በቃል ኪራን የሚያስተሳስር፤ መሬት መቃብር ነው: ጉዞን ሲጨርሱ እፎይ ብለው በጸጋ ክልትው የሚሉበት፤ መሬት የሚተነፍሱት አየር፤ የሚጠጡት ውሃ፤ የሚበሉት ምግብ ነው::*

*በመጨረሻም መሬት **አገር** ነው፤ የማንነት መግለጫ፤ የባሕል ጓዳ፤ የቋንቋ ቃና፤ የሰንደቅ ዓላማ ማስከበሪያ፤ በወዳጁም በጠላቱም ታፍሮ፤ ማንነቱን አስከብሮ እራሱን ቀና፤ ትከሻውን ከፍ አድርጎ በኩራት የሚኖርበት ምድር፤ **መሬት** !!*

*ያለ መሬት ሕይወት ባዶ ናት በውስጧ ምንም የሌለ የተነፈሰች ፊኛ !*

*እንደ እሬት በመምረር፤ እንደ ጭራሮ አድርቃ፤ ቀጭጫ በማቀጨጭ፤ እንደ ከሰል አክስላ፤ በጎስቋላ ጎዳና እያንገጫገጨች ያለ ርህራሄ ወደ መቃብር የምትጎትት ሚርት !*

*ታዲያ ማነው ? ማንነቱ ተሸጦ፤ ባሕሉ ተንዶ፤ ቋንቋው ተረስቶ፤ ሰንደቅ አላማው ተቀዶ፤ ዕትብቱ ከተቀበረበት መሬት በአዘራፊዎች አጋፋሪነት በድንበር ዘለል ዘራፊዎች ሲዘረፍ፤ አንገቱን ሰብሮ፤ ትከሻውን ቀብሮ፤ እራቁቱን ሲያስቀሩት ዝም የሚል ?!*

*ላምባዋ አልቆ ልትጠፋ ጭል ጭል በምትል ኩራዝ: በሚለገስ ብርሃን: በሚተዳደር አገር ውስጥ ያለ ሕዝብ፤ ከዚህ በኋላ የሚመጣው ድቅድቅ ጨለማ መሆኑን በመረዳት፤ ተነስቶ ለኩራዙ የሚሆን ላምባ ያፈላልጋል፤ ወይም በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እንደ ሌሊት ወፍ ተዘቅዝቆ፤ ሰው ከመሆን በታች ዝቅ ብሎ፤ ዝቅዝቅ ኑሮ ይኖራል ከለሊት ወፍ አንሶ !!*

*ጠላቶቹ ቢቻላቸው: ጭል ጭል የምትለዋን ኩራዝ ድርግም አድርገው በማጥፋት: በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየተደናበረ ዳፍንታም ሆኖ እንዲኖር: ከተመኙለት: ሰንበትበት ከማለት አልፎ ከርሟል፤ እናም ምርጫው በድቅድቅ ጨለማ ተዳፍኖ መኖር፤ ወይም በብርሃን ለመኖር ብርሃን ፍለጋ መነሳት ነው::*
*ጎበዝ ! ሰንቶቻችን በጨለማ ላለመኖር ወስነናል ?!*

*የውጪ ወራሪዎች ኢትዮጵያን በጦር ወግተው ቅኝ መግዛት እንደማይችሉ የተረዱት ገና ከጠዋቱ ነበር፤ እንግሊዞች አፄ ቴዎድሮስን ወግተው የዘረፉትን ዘርፈው ሹልክ ብለው የወጡት ኢትዮጵያን ቅኝ ተገዢ ለማድረግ ቢሞክሩ የሚከተላቸውን ጣጣ ስላወቁ ነበር::*

ቀጥሎም የጣሊያን ወራሪ ጦር በአምዬ ምኒሊክ ሠራዊት በአደዋ ድል ሲመታ፤ የመላው ነጭ ዘር ሽንፈት ተደርጎ በመወሰዱ በኢትዮጵያ ላይ ቂም ተቋጥሮ አመቺ ጊዜ በመጠበቅ በማይጨው ጦርነት ተመልሰው ቢመጡም ዕጣቸው አሁንም ሽንፈት ሆነ::

ከዚያም ኢትዮጵያን ድል መምታት የሚቻለው፤ ጦር ሰንቀው፤ ሠራዊት አሰልፈው፤ በመውረር ሳይሆን፤ ተጣመው ባደጉ በገዛ ልጆቿ መሆኑን በመረዳት፤ ጠማሞች ልጆቿን ኮትኩቶ የበለጠ የተጣመሙ ሆነው እንዲያድጉ በማድረግ ይኸው አሁን በ21ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ኢትዮጵያን ለመቀራመት በቁ::

የሚገርመው ከጥንት ባላንጣዎቻችን ባሻገር፡ እንደ ቻይና፤ ሕንድ፤ ቱርክ፤ ሳውዲ አረቢያ፤ ግብፅና ጅቡቲ የመሳሰሉ በቅኝ ተገዢነት የማቀቁ፤ በሙስና የተጨማለቁ አገሮች እንኳን ሳይቀሩ፤ ሕዝባችንን ከመሬቱ በማፈናቀል የመሬታችን ተከራዮች መሆናቸው ሲሆን፤ ከነዚህ ዝርክርክ አገሮች የወደፊት ትርፋችን፤

- አፈሩ ደህይቶ ወደፊት ቢታረስ ፍሬ የማያፈራ መሬት
- አገር በቀል የማምረቻ ፋብሪካዎች፤ ባንኮችን፤ ኢንሹራንሶችን፤...ወዘተ ማዳከም
- ኢትዮጵያዊ ነጋዴዎችን በድንበር ዘለል ነጋዴዎች መገፍተር
- የቆሻሻ ክምችትና፤ ለጤና ጠንቅ በሆኑ ጋዞች በመበከል የዜጎችን ጤና ማቃወስ
- የከባቢ አየር መዛባት በመፍጠር ድርቅና ጎርፍ እንዲበራከት ማድረግ
- ያለው አልበቃ ብሎ፤ ባለው ላይ ሌላ ተጨማሪ ሙስና (ንቅዘት) መጨመር
- የቅጂ ቅጂ ቴክኖሎጂ ጥገኛ በማድረግ፤ እድገትን ማቀጨጭ
- የደን ጭፍጨፋ፤ የአራዊትና የማዕድን ዝርፊያ
- ቻይናዎችና ሕንዶች ጤፍ እንጀራ ሲበሉ እኛ ኢትዮጵያውያን ሩዝ መቀላወጥ
- የተቀራመቱትን መሬት ለማስጠበቅ በሚል በቅጥረኛ ወታደሮች መወረር፤ (በላይቤሪያና በኮንጎ የሚደረገውን የወርቅና የአልማዝ ዘረፋ ያስታውሷል)
- የመረጃ ቴክኖሎጂ (Information Technology) ጥገኛ በመሆናችን፤ የነሱን ፍላጎት ማርካቱ የቀረ ወይም የቀነሰ ዕለት፤ - በወታደራዊ ምስጢሮች፤ በምጣኔ ሃብት፤ በማዕድን፤ በገንዘብ ዝውውር፤ በጤና፤ በውሃ ሃብት ... ወዘተ. በሁሉም መስክ የሚፈጥሩት ምስቅልቅል፤ እጅግ የከፋ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ነው

*የወያኔና የሻ'ቢያ ምኞትም ይኸው እንዲሆን ነው፤ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነት አሻራዎችን በማጥፋት አገራችንን መበታተን ። በቅርቡ በአትሌቶቻችን ላይ የተሰራው ደባ የዚሁ እቅድ አንዱ አካል ነው።*

*በተወዳደሩበት አገር ሁሉ አሸናፊ በመሆን፤ የኢትዮጵያን ባንዲራ ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ በማድረጋቸው፤ ከወያኔ ዓላማ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ፤ እንዲበታተኑ በማድረግ የወያኔ ሰለባዎች ሆነዋል።*

*ሕግ የብዙሃኑን መብት ካላስጠበቀ፤ ሕግ መሆኑ ቀርቶ የገዢው ክፍል የመጨቆኛ መሣሪያ ነው፤ ሰፊው ሕዝብ ደግሞ ይህንን ጨቋኝና አፋኝ ሕግ፤ በሕዝባዊ አመጽ እንዲወገድ ማድረግ ሕገ ወጥ አያሰኘውም፤ ሰብአዊ መብቱ እንጂ።*

***እናም የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ጨቋኝ ሕጎች መቃወም መብቱ ነው!***

***አዘራፊና ዘራፊዎችን በመከላከል፤ ወጣቱ የአገሩ ባለቤት ለመሆን ይነሳ !***

***መናገር፤ መጻፍ፤ የተቃውሞ ሠላማዊ ሰልፍ መጥራት፤ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፤ በጥቅሉ ሕዝብዝዊ እምቢተኝነትን መጠቀም፤ የዲሞክራሲ መብታችን ነው !***

***አገራችንን ከአዘራፊዎችና ከዘራፊዎች መረከብ ያለብን ዛሬ እንጂ ነገ አይደለም !***

***ከንፈር በመምጠጥ፤ የኛን ሥራ ለእግዚአብሔር መስጠት፤ እሱ ያመጣውን እሱ ይመልሰው እያሉ በፈጣሪ ማሳበብ ከሃላፊነት መሸሽ ነው !***

***መብታችንን በእርጥባን መልክ እንዲሰጡን ነፌችን መለመኑ ይብቃ !***

## *ማሳረጊያ:*

***እዚህ ጋ ስደርስ ከቃላት ይልቅ ባንድ ወገን የወገኖቻችንን ስቃይ፤ በሌላ ወገን ደግሞ የዘራፊዎችን ሥራ እጅግ በላቀ መልኩ ስለሚገልጹ፤ እነዚህን ምስሎች መረጥኩ።***
***ለመሆኑ ምን እየሠራህ ነው ?***
***ምን እየሰራሽ ነው ?***
***ምን እየሠራችሁ ነው ?***
***እስከመቼ ?***
***ብለው ሁላችንንም ይጠይቃሉ፤ መልሳችን ምን ይሆን ?***

 




*ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !*

*እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!*

*መስከረም 17 / 2004 ዓ.ም.   (September 28/ 2011)*